

# የ DCPS መጻዒ ይቅረጹ

ለዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ማኅበረሰብ፣

እኔ በመጀመሪያ በፌብሩዋሪ 1 እንደ ቻንስለር ሆኜ ወደ ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) ስመጣ በማደግ ላይ ወዳለች ዲስትሪክት እና ከተማ እየመ ጣሁ እንዳለሁ ዐውቄው ነበር። ወደ DCPS ስመጣ ትምህርት ቤቶቹ እያሳዩ ባለው ዕድገት ብቻ ሳይሆን ወደፊት ይበልጥ ለማደግ ባላቸው ዕምቅ አቅም ተደ ስቼያለሁ። ከቅድመ-መውዓለ ሕጻናት ተማሪዎች እስከ የከተማዋ አመራሮች ድረስ እዚህ የተዋወቅኳቸው ሰዎች ባላቸው ተሰጥዖ እና ለሥራ ባላቸው ጥልቅ ፍቅር በጣም አስደምመውኛል።

በ2012፣ DCPS ከፍተኛ ወኔን የሚጠይቅ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ - ካፒታል ኮሚትመንት (Capital Commitment) በመባል የሚታወቁ አምስት ግቦች ያሉትን ዕቅድ ጀምሮ ነበር። ከአምስት ዓመታት በኋላ፣ አካዳሚያዊ ሥራ አፈጻጸም ብቃት ከፍ ብሏል፣ የተመራቂ ብዛት ጨምሯል፣ የተመዝጋቢ ብዛት ጨምሯል፣ የተማሪዎች እርካታ መጠን ጨምሯል እና የእኛ ዲስትሪክት ሊፈጽመው የሚችለውን አዲስ ራዕይ የምንነድፍበት ጊዜ ደርሷል። ሁሉንም የእኛ ትምህርት ቤቶች ወደ ቀጣዩ ከፍተኛ ደረጃ የምንወስድበት ጊዜ አሁን ነው።

ስለ DCPS ያሉኝን ዕቅዶች እንድናገር በተደጋጋሚ ተጠይቄያለሁ። እናም የራሴ የሆኑ በርካታ ሐሳቦች አሉኝ። ሆኖም ግን እናንተ የ DCPS ማኅበረሰብ አባላት የእናንተ ልጆች እና ትምህርት ቤቶች አቅማቸውን ሁሉ አውጥተው ወደ የመጨረሻው የተሻለ ደረጃቸው እንዲደርሱ ከማንም በተሻለ ምን መደረግ እንዳለበት ታውቃችሁ።

በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት ውስጥ፣ ለ DCPS ምን ራዕይ እንዳልዎት ለማወቅ ጥያቄ እጠይቃለሁ። እያንዳንዱ ተማሪ፣ ወላጅ እና መምህር ወደ ትምህርት ቤታቸው እንዲመጡ፣ ሲመጡም ቤታቸው ሆኖ እንዲሰማቸው ለማድረግ፣ ለሥራ ለማነሳሳት እና ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ ምን መደረግ አለበት? በእኛ ዲስትሪክት በሁሉም መስፈርቶች እንዴት አድርገን ስኬታማነትን እና ርትዓዊነትን ማስፈን እንችላለን?

ከቤተሰቦች እና ተቋማት ጋር በመላ ከተማዋ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች እየተገኘሁ ውይይት አደርጋለሁ፣ በእያንዳንዱ ክንፍ ያሉትን ተሳትፎ ማድረጊያ ክፍለ ጊዜዎች እመራለሁ እንዲሁም የእኛን የእምነት ድርጅቶች፣ ሰፈሮች እና የንግዱ ማኅበረሰብ መሪዎች እተዋወቃለሁ። DCPS በተጨማሪ የይጻፉ ዘመቻን ስለ ሚያዘጋጅ እያንዳንዱ ሰው ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ቅድሚያ መሰጠት ያለባቸውን ነገሮች ለማሳወቅ ዕድሉ ይኖረዋል።

እውነተኛ ግብረ መልስ እንደሚሰጡ እና ሊሆኑ አይችሉም የሚባሉ ሕልሞችዎን ሳይቀር እንደሚያካፍሉን በእርስዎ እተማመናለሁ። እኛ DCPS ነን፣ እንደ ላይ ሆነንም ይህን ማድረግ እንችላለን።

ከማክበር ሰላምታ ጋር፣

አንትዋን ዊልሰን (Antwan Wilson)
የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ቻንስለር



## DCPS ከቤተሰቦች እና ማኅበረሰብ አባላት ጋር በመሆን የ DCPS ተማሪዎችን ለማገዝ በጋራ ይሠራል።

በእርስዎ ያሉበት ክፍል የሚከተለውን ለማድረግ ከእኛ ጋር ይሁኑ፡-

**ድምፆን ያሰሙ** ለእርስዎ ልጅ እና ለትምህርት ቤቱ ቅድሚያ መሰጠት ስላለባቸው ነገሮች።

**ተሳትፎ ያድርጉ** ከእኛ ሌሎች የማኅበረብ አባላት ጋር።

**ይተዋወቁ** ከቻንስለር አንትዋን ዊልሰን ጋር።

## ተሳትፎ ማድረጊያ ክፍለ ጊዜዎች

**ማክሰኞ፣ ማርች 7 በ Ron Brown HS**
4800 Meade Street, NE • Ward 7

**ሐሙስ፣ ማርች 16 በ Roosevelt HS**
4301 13th Street, NW • Ward 4

**ማክሰኞ፣ ማርች 21 በ Luke C. Moore HS**
1001 Monroe Street, NE • Ward 5

**ሰኞ፣ ማርች 27 በ Deal MS**
3815 Fort Drive, NW • Ward 3

**ሐሙስ፣ ኤፕሪል 6 በ Turner ES**
3264 Stanton Road, SE • Ward 8

**ማክሰኞ፣ ኤፕሪል 11 በ Eastern HS**
1700 East Capitol Street, NE • Ward 6

**ሐሙስ፣ ኤፕሪል 13 በ Columbia Heights EC**
3101 16th Street, NW • Ward 1

**ሰኞ፣ ኤፕሪል 24 በ SWW @ Francis-Stevens**
2425 N Street, NW • Ward 2

**ሁሉም ክፍለ ጊዜዎች ከምሽቱ 6:30 እስከ ምሽቱ 8:30 PM ድረስ ይከናወናሉ። ቀለል ያለ የእራት መስተንግዶ እና የልጆች ክብካቤ አገልግሎት ይሰጣል።**

## የተሳትፎ ማድረጊያ ክፍለ ጊዜ ላይ መሳተፍ አይችሉም? በእኛ ይጻፉ ዘመቻ ላይ ይሳተፉ!

መስመር ላይ (ኦን ላይን) EngageDCPS.org

ኢሜይል ofpe.info@dc.gov

ፖስታ አድራሻ DC Public Schools
c/o Office of Family and
Public Engagement
1200 First Street, NE
Washington, DC 20002




# 2012-2017 CAPITAL COMMITMENT

### ግብ 1 የስኬታማነትን መጠን ማሻሻል

ከተማሪዎቻችን ቢያንስ 70% ያህሉ በ 2016-2017 ላይ በንባብ ትምህርት እና ሒሳብ ብቁ ተማሪዎች ይሆናሉ። በ 2016-2017 ላይ የላቁ ተማሪዎቻችንን ቁጥር እጥፍ እናደርገዋለን፤ ይኸውም ከ 3,800 በላይ በንባብ ትምህርት እና ከ 4,700 በላይ በሒሳብ የላቁ ተማሪዎች ይኖሩናል።

### ግብ 2 እየታገሉ ባሉ ትምህርት ቤቶች ላይ መውዓለ ንዋይን ማፍሰስ

ዝቅተኛ አፈጻጸም ብቃት ያላቸው 40 የእኛ ትምህርት ቤቶች በ 2016-2017 የብቃት ደረጃውን በ 40 በመቶ ነጥቦች ይጨምራሉ።

### ግብ 3 የተመራቂዎችን ብዛት መጨመር

በ 2016-2017 ወደ 9ኛ ክፍል ከሚገቡ ተማሪዎች መካከል ቢያንስ 75% ያክሉ በአራት ዓመታት ውስጥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጨርሰው ይመረቃሉ።

### ግብ 4 የእርካታ መጠንን መጨመር

በ 2016–2017 ከተማሪዎች 90% ያክሉ ትምህርት ቤታቸውን እንደሚወዱ ይናገራሉ።

### ግብ 5 የተመዝጋቢ ብዛትን መጨመር

DCPS የተመዝጋቢ ብዛቱን በመጨመር በ 2016-2017 ከ 50,000 ተማሪዎች በላይ እንዲሆን ያደርጋል።

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

dcps.dc.gov/engage ላይ ተጨማሪ ይረዱ